# ቁናው ቁናዬ ነው!



እኒያ ጥንተ አበዎች የተፈላሰፉ፣
ዓለምን ታዝበው በቅኔ ሲዘርፉ፣
የበደል መስፈሪያ ቁና ናት ይላሉ፡፡

ራስን ፈትሸው ሲገቡ ንስሃ፣
እንዲህ ይሉ ነበር አባቶች በጦቢያ፣
"ሰው በድዬ ነበር እኔም እንደ ዋዛ፣
ቁናው ቁናዬ ነው ትንሽ ዙሩ በዛ!"

ንስሃ እሚገባ ዛሬ ሰው ጠፋና፣
በደል መስፈር ቀረ በስንደዶ ቁና!

ተማክረው ተባብረው እናት የነከሱ፣
ዛሬ በመንጋጋ እርስ በርስ ሲባሉ፣
ቁናው ቁናዬ ነው ማለትን እረሱ፡፡

አምና ሰርቀው ውጠው ዘንድሮ ሲተፉ፣
ዘረፉን እያሉ ሌሎችን ያማሉ፣
በቁና እሚሰፍር ይሉኝታ ስላጡ፡፡

ሌሎች ሲታሰሩ ይበል ይሁን ያሉ፣
ስንቶች ሲገረፉ ጅራፍ ያቀበሉ፣
ሺዎች አሰድደው ዘርፈው የከበሩ፣
ሰማእት ሲረሸኑ ፌስታ የጨፈሩ፣
ዛሬ ቁናው ሲደርስ ጨርቅ ጥለው ሄዱ፡፡

በሰፈሩት ቁና መሰፈር እንዳይቀር፣
ትንሽ ሰከን ብለው ቢያስቡት ቀደም ሲል፣

ወደ ላይ ባልሸኑ ጠጥተው የደም ሴል፡፡

መንደሩ ሰፈሩ ሰላም እሚሆነው፣
በአገር ዜጋ በቅሎ አሽቶ እሚያፈራው፣
በሰፈሩት ቁና መሰፈርን አውቀው፣
በደል ግፍ መስራትን ተጦሙ ብቻ ነው፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
የካቲት ሁለት ሺ አስራ ሶስት  ዓ.ም.